https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No. 23
ADDIS ABABA, 7th March 2017

**ማውጫ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፱/፪ሺ፱ ዓ.ም

የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………ገፅ ፱ሺ፭፻፵፯

**CONTENT**

Council of Ministers Regulation No.399/2017

Foreign Service Officers Administration Council of Ministers Regulation……………………………………………page 9547

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፱/፪ሺ፱

## የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን እና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና በውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭ አንቀጽ ፶፮(፩) መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፺፱/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

Council of Ministers Regulation No.399 /2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION FOR THE ADMINISTRATION OF FOREIGN SERVICE OFFICERS

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916/2015 and Article 56(1) of the Foreign Service Proclamation No.790/2013.

### PART ONE

### GENERAL

**1. Short Title**

This Regulation may be cited as the "Foreign Service Officers Administration Council of Minister Regulation No. 399 /2017".

https://chilot.me



ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፪.ትር**

፩/ "አዋጅ" ማለት የውጭ ግንኙነት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር ፯፻፺/፪ሺ፭ ነው፤

፪/ "የሙያ መሰላል" ማለት በአዋጁ አንቀጽ ፱ እስከ ፲፪ የተመለከቱት የዲፕሎማቲክ ምድብ ደረጃዎች ናቸው፤

፫/ "በሙያ መሰላል የሚደረግ ዕድገት" ማለት የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ከአንድ የሙያ መሰላል ወደሚቀጥለው ከፍ ያለ መሰላል የሚሸጋገርበት ሥርዓት ነው፤

፬/ "በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ ፈጣን የሙያ መሰሳል ዕድገት" ማለት በአንድ ጊዜ ሁለት የሙያ መሰላል ዕድገት የሚሰጥበት ሥርዓት ነው፤

፭/ "የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት" ማለት በአዋጁ፣ በዚህ ደንብ እና አግባብነት ባለው የፌደራል መንግስት ሰራተኞች ሕግ መሠረት የሚደረግ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ነው፤

፮/ "የሰው ሀብት ማኔጅመንት" ማለት የሚኒስቴሩ የሰው ሀብት ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ነው፤

፯/ "የሥራ አመራር ምክር ቤት" ማለት በአዋጁ አንቀፅ ፶(፩)□(ሀ) መሰረት የተቋቋመ ስትራቴጅያዊ አመራር የሚሰጥ የውጭ ግንኙነት አካል ነው፤

፰/ "የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ" ማለት በአዋጁ አንቀፅ ፶(፩)(ለ) መሰረት የተቋቋመ የውጭ ግንኙነት አካል ነው፤

፱/ "የቅሬታ ሰሚ ቦርድ" ማለት በአዋጁ አንቀፅ ፶(፩)(ሐ) መሰረት የተቋቋመ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሰራተኞች የሚያቀርቡትን አቤቱታ

**2. Definition**

In this Regulation:

1/ "Proclamation" means the Foreign Service Proclamation No.790/2013;

2/ "career ladder" means the diplomatic service categories specified under Articles 9-12 of the Proclamation;

3/ "career ladder promotion" means a mechanism for the promotion of a diplomatic service officer from one career ladder to the next higher career ladder;

4/ "accelerated career ladder promotion" means the mechanism in which two career ladder promotion is given at once;

5/ "performance evaluation result" means the performance evaluation of a diplomatic service officer in accordance with the Proclamation, this Regulation and appropriate Federal civil service laws;

6/ "human resource management" means the Human Resource Management Directorate General of the Ministry;

7/ "management council" means a Foreign Service organ of the Ministry established under Article 50(1)(a) of the Proclamation which gives strategic leadership;

8/ "examination administration board" means a Foreign Service organ of the Ministry established under Article 50(1) (b)of the proclamation;

9/ "Grievance Hearing Board" means a Foreign Service organ of the Ministry established under Article 50(1) (c) of the Proclamation to hear and investigate grievances submitted by the Foreign Service officers and submit its recommendation to the Minister;

https://chilot.me



ጥርመር የውሳኔ ሃሳብ ለሚኒስትሩ የሚያቀርብ የውጭ ግንኙነት አካል ነው፤

፲/ በአዋጁ የተሰጡ ትርጓሜዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## ክፍል ሁለት

## የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ ምልመላ፣ የሙከራ ጊዜ ቅጥር፣ ሥልጠና እና ምዘና

### ፫.የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ምልመላ

፩/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ ምልመላ በአዋጁ አንቀፅ ፳፩ እና ፳፪ በተደነገገው መሰረት ዕውቀትና ችሎታን መሰረት ባደረገ ግልፅ ውድድር የሚፈፀም ይሆናል።

፪/ ለሙከራ ጊዜ ቅጥር ለተወዳዳሪዎች የሚሰጠው ፈተና ውጤት በሚኒስቴሩ ከተገለጸበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ድረስ ጸንቶ ሊቆይ ይችላል።

### ፬. የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ

፩/ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የተቀመጡትን መስፈርቶች ያሟላ እና በፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ የሚሰጠውን ፈተና ያለፈ አመልካች የዲፕሎማቲክ አገልግሎት የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ሆኖ ይቀጠራል፡፡

፪/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም የሚሰጠውን ስልጠና ከመጀመሩ በፊት የቅጥር ውል ይፈጽማል።

፫/ ለሙከራ ጊዜ ሠራተኛው የሥራ መደቡ መጠሪያ፣የተመደበበትን ደረጃ ደሞዙንና ሥራውን የሚጀምርበትን ቀን የሚገልጽ የሙከራ ቅጥር ደብዳቤ በሚኒስትሩ ወይም ሌላ ስልጣን በተሰጠው የሥራ ክፍል ኃላፊ ተፈርሞ ይሰጠዋል።

፬/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሙከራ ጊዜ ሰራተኛ የሙከራ ጊዜ ቅጥር ለሁለት ዓመት

10/ the definitions provided under the Proclamation shall apply.

## PART TWO

## PROBATION PERIOD, RECRUITMENT, TRAINING AND EVALUTION OF A DIPLOMATIC SERVICE SECTOR OFFICER

### 3. Recruitment of Diplomatic Service Officer

1/ Any Recruitment of officer of the diplomatic service sector shall be conducted transparently in accordance with Articles 21 and 22 of the Proclamation based on merit and competence.

2/ The examination result of applicants may remain valid for a period of one year from the date of its announcement by the Ministry.

### 4. Probationer

1/ An applicant, who passes the examination administered by the Examinations Administration Board and fulfils the criteria prescribed under the Proclamation and this Regulation shall be employed as a probationer in the diplomatic service sector.

**2/** The probationer shall conclude an employment contract before commencing training at the Foreign Service Training Institute

3/ The probationer shall be provided with a letter signed by the Minister or other authorised head of a section stating the title, grade, position, salary and date of commencement of his employment.

4/ The period of probation of a diplomatic service officer shall be two years and six months.

https://chilot.me



ወር ይሆናል፡፡

### ፬. ለሙከራ ጊዜ ሠራተኞች ስለሚሰጥ ስልጠና

፩/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በሚኒስቴሩ የሚሰጠውን የአንድ አመት የንድፈ ሃሳብና የአንድ አመት ከስድስት ወር የሥራ ላይ ሥልጠና መውሰድ አለበት፡፡

፪/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ የሁለት ዓመት ተኩል የሙከራ ጊዜውን ካጠናቀቀ በኂላ የዲፕሎማቲክ ንድፈ ሃሳብ ስልጠና የወሰደበትን ጊዜ ያህል በሚኒስቴሩ ውስጥ የማገልገል ግዴታ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተመለከተውን ግዴታ ያለበቂ ምክንያት ያልተወጣ ሠራተኛ ሚኒስቴሩ ለስልጠና ያወጣውን ወጭ ይከፍላል፡፡

### ፭.ቃለ መሃላ

“ማንኛውም የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ሥራ ከመጀመሩ በፊት የሚከተለውን ቃለ መሃላ ይፈጽማል፡፡ *“እኔ ……………………. የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሰራተኛ ሆኜ ስቀጠር የተጣለብኝን ኃላፊነት በታማኝነትና እና በቅንነት ለማከናወን፣ በማንኛውም ጊዜ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስትና የአገሪቱን ሕጎች ለማክበር፣ የመንግስትን ፖሊሲዎች ለማስፈጸም፣ የሀገሬን ብሄራዊ ጥቅም ለማስጠበቅና በሥራዬ ምክንያት ያወቅኂቸውን ምስጢራዊ የሆኑ ማናቸውንም ዓይነት ሰነዶችና መረጃዎች ላልተፈቀደለት አካል በማንኛውም መልኩ ላለመግለጽ ቃል እገባለሁ፡፡”*

### ፮. የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ የሥራ ላይ ሥልጠና ምዘና

፩/ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ የሥራ ላይ ስልጠና ምዘና ዓላማ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛውን ሙያዊ ብቃት፣ ክህሎት እና በአዋጁ አንቀጽ ፵፪ ለተጠቀሱት የሥነ-ምግባር መርሆዎች ያለውን ተገዢነት

### 4. Training For Probationers

1/ Any probationer must attend a one year theoretical training and one year and six months of on job training offered by the Ministry.

2/ Any probationer after completion of the two years and six months probation period has the obligation to serve the Ministry for a duration which is equivalent to the time spent at the Foreign Service Institute.

3/ A probationer who fails to discharge the obligation stipulated under sub-article (2) of this Article without a sufficient reason, shall reimburse the cost incurred by the Ministry for his training.

### 5. Oath

Any diplomatic service officer shall, before the commencement of his work, take the following oath.

*“I……………..solemnly swear to carry out my duties with due diligence and integrity, to respect the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and other laws of the country at all times, to safeguard the national interest of my country, to execute government policies and not to disclose any confidential information and documents which I came to know by reason of my duties to any other non-authorized person.”*

### 6. On Job Training Evaluation of a Probationer

1/ The purpose of performance evaluation of a probationer shall be to evaluate the professional competence of the probationer, his skill and his observance of the ethical

https://chilot.me



…መዘን ነው::

፪/ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲያገኝ የተመደበበት የሥራ ክፍል ኃላፊ:-

ሀ) የሙከራ ጊዜ ሠራተኛውን የሚከታተል የቅርብ አሠልጣኝ ይመድባል፤

ለ) ሥልጠናውን በተገቢው መከታተሉን ያረጋግጣል፤

ሐ) አፈፃፀሙን ይመዝናል፤

መ) የምዘና ውጤቱን የሚመለከተው የስራ ክፍል እና የሙከራ ጊዜ ሠራተኛው እንዲያውቁት ያደርጋል::

፫/ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት አሰጣጥ በፌደራል መንግስት ሠራተኞች ሕግ መሠረት የሚሰጥ ይሆናል::

**፰. ለሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ስለሚደረግ ድጋፍ**

፩/ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛው በእያንዳንዱ ምዘና ቢያንስ አጥጋቢ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ ውጤት ማስመዝገብ ይኖርበታል::

፪/ በስልጠና ወቅት ዝቅተኛ የአፈፃፀም ውጤት ያስመዘገበ የሙከራ ጊዜ ሰራተኛ በአዋጁ አንቀጽ ፳፭ (፫) መሠረት በአሰልጣኙ ወይም በቅርብ ኃላፊው ድጋፍና ክትትል እየተደረገለት የሙከራ ጊዜው ለስድስት ወራት ሊራዘምለት ይችላል::

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የሙከራ ጊዜው የተራዘመለት የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በተራዘመው የሙከራ ጊዜ አጥጋቢ ወይም ከዚያ በላይ የሥራ አፈጻጸም ውጤት ካላገኘ ከስራ ይሰናበታል::

obligations prescribed under Article 42 of the Proclamation.

2/ The head of the section where the probationer is assigned for on job training, shall:

a) assign a mentor;

b) ensure that the training is properly being provided;

c) evaluate the performance of the probationer and

d) inform the result of the evaluation to the appropriate section and the probationer.

3/ The performance evaluation of a probationer shall be graded in accordance with relevant Federal Civil Service law.

**8. Support to a probationer**

1/ The probationer shall at least score a “satisfactory or above” result upon each evaluation.

2/ The probation period of a probationer who has scored “low” on his evaluation may be extended for an additional six months subject to close assistance and follow up by his mentor or immediate supervisor pursuant to sub-article (3) of Article 25 of the Proclamation,.

3/ A probationer whose probation period has been extended pursuant to sub-article (2) of this Article shall have his contract terminated if he fails to score an evaluation result of “satisfactory or above” during the extended period.

https://chilot.me





**፱.ቋሚ ሠራተኛ ስለመሆን**

፩/ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ቋሚ ቅጥር በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም በሚወስደው በእያንዳንዱ ሥልጠና መጨረሻ በሚሰጡት ፈተናዎች፣ በስልጠና ማጠናቀቂያ በሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ፈተና እና በሥራ ላይ ሥልጠና ወቅት በቅርብ አሠልጣኙ በሚሰጠው ውጤት ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በእያንዳንዱ ምዘና ቢያንስ “አጥጋቢ” ውጤት በማስመዝገብ ያጠናቀቀ የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ በመሆን አንድ ደረጃ ከፍ ብሎ ሚኒስቴሩ በሚመድበው ቦታ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

፫/ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ቋሚ የሆነ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ይሰጠዋል፡፡

**፲. ቅጥርን ስለመሰረዝ**

ማንኛውም በሐሰት ወይም በተጭበረበረ የትምህርት ማስረጃ ወይም የሥራ ልምድ ማስረጃ በማቅረብ ወይም ሥልጣን በሌለው አካል በተሰጠ ማስረጃ ወይም አዋጁን እና ይህን ደንብ ወይም ሌላ ማናቸውንም ሕግ በመተላለፍ የተፈጸመ የሥራ ቅጥር በማንኛውም ጊዜ ይሰረዛል፡፡

**፲፩. በውጭ ግንኙት አገልግሎት ዘርፎች መካከል ስለሚደረግ የሰራተኛ ዝውውር**

፩/ ሚኒስቴሩ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ መሰረት የሠራተኞችን የትምህርት ዝግጅትና የአገልግሎት ዘመን፣ የሙያ ብቃትና ክህሎት እንዲሁም የስራ አፈፃፀም ውጤትን መሰረት በማድረግ ከአንዱ የስራ ዘርፍ ወደሌላው ሊያዛውር ይችላል፡፡



**9. Permanent Diplomatic Service Officer**

1/ Permanent appointment of a probationer at diplomatic service sector shall be determined based on the result of each examination taken at the end of each course received at the Foreign Service Training Institute, the result of the examination given at the end of the theoretical training and the result of the assessment carried out during the on job training by the his mentor.

2/ A probationer who completes his probation period with at least a “satisfactory” result on each evaluation of the probation period, shall be a permanent diplomatic service officer and work in a post assigned by the Ministry after being promoted to the next higher career ladder.

3/ A probationer, who becomes a permanent Diplomatic Service Officer by virtue of sub-article (2) of this Article, shall be provided with a letter to that effect.

**10. Termination of Employment**

Any employment made on the basis of false or forged representation regarding educational qualification or work experience or certificates issued by unauthorized person or in contravention of the Proclamation, this Regulation or any other law shall be terminated at any time.

**11. Transfer of Personnel Between Foreign Service Sectors**

1/ The Ministry may transfer its employees from one sector to the other taking into account the educational qualification and experience, professional competence and skill, as well as

https://chilot.me



፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫(፫) መሰረት በደረጃ ዕድገት መሙላት ያልተቻለ ክፍት የዲፕሎማቲክ አገልግሎት የሥራ ቦታ በአዋጁ አንቀጽ ፳፱ እና በዚህ ደንብ መሰረት ከአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ወደ ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ በሚደረግ ዝውውር ሊሞላ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ከአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ወደ ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚዛወር ሰራተኛ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፤

ሀ) በፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ የሚሰጠውን ፈተና ማለፍ፤

ለ) በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት፤

ሐ) ከከባድ የዲሲፕሊን እርምጃ ነጻ መሆን፤

መ) ለዝውውር ዕጩ ከመሆኑ በፊት ከተከናወኑ አራት ተከታታይ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቶች በሁሉም ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ማስመዝገብ፤

ሠ) በአስተዳደርና ቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ በፕሮፌሽናል ሳይንስ የአገልግሎት ዓይነት ቢያንስ ለአምስት ዓመት ያገለገለ መሆን፡፡

፬/ ከአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ወደ ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚደረግ ዝውውር ዝቅተኛው የሙያ ደረጃ ሶስተኛ ጸሐፊ ሲሆን ከፍተኛ የሙያ ደረጃ አንደኛ ጸሐፊ ይሆናል፡፡

performance evaluation result in accordance with Article 29 of the Proclamation.

2/ Without prejudice to sub-article (1) of this Article, a vacant diplomatic service post which is not filled by a promotion as per Article 23(3) of the Proclamation may be filled by a transfer from administrative and technical service sector based on Article 29 of the Proclamation and this Regulation.

3/ An employee to be transferred from administrative and technical service sector to the diplomatic service sector according to sub-article (2) of this Article shall:

a) pass the examination given by the Examination Administration Board;

b) fulfil the requirements stipulated under Article 21 (1) of the Proclamation;

c) have no any record of rigorous disciplinary measures;

d) score a high result in four consecutive performance assessments carried out before he became a candidate for a transfer and

e) serve at least five years in administrative and technical service sector in a professional science service.

4/ The minimum career rank for an employee transferred from administrative and technical service sector to diplomatic service sector shall be third secretary while the highest career rank shall be first secretary.

https://chilot.me



፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ከአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ወደ ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የተዛወረ የአስተዳደርና የቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም የሚሰጠውን የአንድ ዓመት የንድፈ ሀሳብ ሥልጠና እና በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚሰጠውን የስራ ላይ ስልጠና መውሰድ አለበት፡፡

፮/ ከአስተዳደርና ከቴክኒክ አገልግሎት ዘርፍ ወደ ዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የተዛወረ ሰራተኛ በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የደረጃ ዕድገት የሚያገኘው በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ እና ተከታዮቹ አንቀጾች በተደነገገው መሰረት ይሆናል፡፡

## ፲፪. <u>ከአታሼ ደረጃ በላይ ለሆነ ክፍት የሥራ ቦታ ስለሚደረግ ቅጥር</u>

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፫ (፬) መሠረት ከአታሼ ደረጃ በላይ የሆነ ክፍት የሥራ ቦታ በስራ አመራር ምክር ቤቱ ውሳኔ በአዋጁ አንቀጽ ፳፩ እና ፳፪ በተደነገገው መሰረት ዕውቀትና ችሎታን መሰረት ባደረገ ግልፅ ውድድር በቅጥር ሊሞላ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተቀጠረ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት የሙከራ ጊዜ ሠራተኛ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም የሚሰጠውን የንድፈ ሀሳብ ስልጠና እና በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚሰጠውን የሥራ ላይ ስልጠና መውሰድ አለበት፡፡

## ፲፫. <u>ርቱዓዊ ተሣትፎን ስለማረጋገጥ</u>

በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ሆኖ ለመቀጠር መሟላት ያለባቸው የሙያ ብቃት እና አግባብነት ያላቸው



5/ An employee who is to be transferred from administrative and technical service sector to diplomatic service sector shall attend the one year theoretical training provided at the Foreign Service Training Institute and undertake the on job training in the diplomatic service sector.

6/ The promotion of an employee transferred from administrative and technical service sector to diplomatic service sector shall be in accordance with Article 20 and the subsequent provisions of this Regulation.

## 12. <u>Filling of Vacant Positions above the Category of Attaché</u>

1/ Vacant posts above the rank of attaché in accordance with article 23(4) of the Proclamation shall be filled in accordance with Article 21 and 22 of the Proclamation by the decision of the management council based on merit and competence following a transparent process.

2/ A person employed as a probationer in the diplomatic service sector by virtue of sub article 1 of this Article, shall take training at the Foreign Service Training Institute and undertake the on job training in the diplomatic service sector.

## 13. <u>Ensuring Equitable Representation</u>

Without prejudice to the professional competence and relevance requirements for employment as a diplomatic

https://chilot.me



፱ሺ፭፻፶፭ ፉ እንደተጠበቁ ሆነው በሚኒስቴሩ ውስጥ አነስተኛ ተዋጽኦ ያላቸውን ብሔረሰቦች፣ አካል ጉዳተኞችንና ፆታን ከግምት በማስገባት ርቱእዊ ተሳትፎን የማረጋገጥ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

**፲፬. ተስማሚነት**

፩/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን በሙሉ ያሟላ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዘርፍ ዕጩ ተቀጣሪ ለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሥራ ያለውን ተስማሚነት ለማረጋገጥ የኋላ ታሪኩን፣ የተደበቀ ማንነት አለመኖሩን፣ በተለያዩ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ጫና ሥር ያልወደቀ መሆኑን፣ ለተለያዩ ጎጂ ሱሶችና ባህሪያት ያልተጋለጠ መሆኑን፣ ከማንኛውም ወንጀል ነፃ መሆኑን፣ ምስጢር ጠባቂነቱን እና አጠቃላይ የሚሰጠውን አገራዊ ተልዕኮ በታማኝነት ሊወጣ የሚችል መሆኑን ማጣራት አለበት፡፡

፪/ በውጭ ግንኙነት አገልግሎት ዘርፎች የሚደረገውን የቅድመ እና ቀጣይነት ያለው የድህረ ቅጥር ተስማሚነት በሚመለከት ሚኒስቴሩ መመሪያ ያወጣል፡፡

**ክፍል ሦስት**

**ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና እና ሥልጠና**

**፲፭. ስለ ሥራ አፈፃፀም ምዘና**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፰ (፩) መሠረት የሚደረግ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ደረጃ አግባብነት ባለው የፌደራል መንግስት ሰራተኞች ሕግ እና በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መስፈርት መሰረት ይሰጣል፡፡

፪/ እያንዳንዱ የሥራ ክፍል የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞችን የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ለሚመለከተው የስራ ክፍል ያቀርባል፡፡ ዝቅተኛ እና

service officer, in accordance with the Proclamation and this Regulation a mechanism that ensures equitable representation taking into account the nationalitie 9555 low representation in the Ministry, persons with disabilities and gender.

**14. Suitability**

1/ To verify suitability of a candidate who fulfils all the other requirements for employment, the Ministry shall investigate the back ground of the candidate, that there is no concealed identity, that he is not under any influence of different internal and external forces, that he is not addicted to different harmful substances and behaviours, that he is free of any criminal records, that he is capable of keeping confidential information, and in general that he is capable of accomplishing his national missions with loyalty.

2/ The Ministry shall issue a directive on the pre-employment and continuous post-employment suitability in the Foreign Service sectors.

**PART THREE**

**PERFORMANCE EVALUATION AND TRAINING OF PERMANENT DIPLOMATIC SERVICE OFFICERS**

**15. Performance Evaluation**

1/ The performance evaluation of a diplomatic service officer conducted pursuant to Article 28(1) of the Proclamation and shall be graded in accordance with the relevant Federal Civil Service laws and according to the criteria set by the Ministry of Public Service and Human Resource Development

2/ Every diplomatic service sector shall submit the

https://chilot.me



. . . .ሥራ አፈፃፀም ያስመዘገቡ ሠራተኞች ውጤት በሥራ አመራር ምክር ቤቱ መፅደቅ አለበት:: ምክር ቤቱ ውጤቱን ውድቅ ካደረገው ሰራተኛው እንደገና ስለሚመዘንበት አሰራር ውሳኔ ይሰጣል::

**፲፮. ስለዝቅተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት**

፩/ ቋሚ የዲኘሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ በተመደበበት ሥራ ላይ ዝቅተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ካመጣ የሥራ አፈፃፀሙን እንዲያሻሽል የቅርብ ድጋፍ ይደረግለታል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በተደረገለት ድጋፍ በቀጣዩ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ቢያንስ አጥጋቢ ውጤት ካላመጣ እና ውጤቱ በሥራ አመራር ምክር ቤቱ ከፀደቀ በችሎታ ማነስ ምክንያት ከሥራ ሊሰናበት ይችላል::

**፲፯. ለቋሚ የዲፐሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ስለሚሰጥ ሥልጠና**

፩/ ሚኒስቴሩ ቋሚ የዲፐሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ስለሚሰለጥኑበት አሰራር ከውጭ ግንኙነት አገልግሎት ማሰልጠኛ ተቋም ጋር በመመካከር ዕቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ያደርጋል::

፪/ ማንኛውም ቋሚ የዲፐሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ከሚኒስቴሩ ወጪ ከስድስት ወር በላይ ለሆነ ጊዜ ስልጠና ከወሰደ ለሰለጠነበት ጊዜ ያህል በሚኒስቴሩ ውስጥ የማገልገል ግዴታ አለበት::

**ክፍል አራት**

**በሙያ መሰላል የሚደረግ ዕድገት**

**፲፰. በሙያ መሰላል የሚደረግ ዕድገት መስፈርቶች**

፩/ ማንኛውም ቋሚ የዲፐሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ በዚህ ደንብ ውስጥ ለእድገት የሚያበቁ ሁኔታዎችን ሲያሟላ ወደ ቀጣዩ የሙያ መሰላል

performance evaluation results of the diplomatic service officers to the appropriate sectors. The Management Council shall approve the r… officers who scored Low and Outstanding. If the Management Council disapproves the result, it shall give a decision on how the officer shall be re-evaluated.

**16. Low Performance Evaluation Result**

1/ A permanent diplomatic service officer whose performance evaluation is “low” shall receive a close assistance to improve his performance.

2/ An officer is unable to score at least a satisfactory result, on the next evaluation period after the special assistance and if the result is approved by the Management Council, the officer may be dismissed on the ground of incompetence.

**17. Training for Permanent Diplomatic Service Officers**

1/ The Ministry shall, in consultation with the Foreign Service Training Institute, prepare a plan on the training of permanent diplomatic service officers get trainings within and outside the country.

2/ Any permanent diplomatic service officer, who received training for more than six months covered by the Ministry, shall serve the Ministry for a duration equivalent with the length of the training.

**PART FOUR**

**CAREER LADDER PROMOTION**

**18. Criteria for a Career Ladder Promotion**

1/ Any permanent diplomatic service officer shall be

https://chilot.me



 ኀማደግ ብቁ ይሆናል፡፡

፪/ የሙያ መሰላል ዕድገት በዋናነት በሠራተኛው የሥራ አፈጻጸም ውጤት መሠረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

፫/ ማንኛውም ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ከአንድ የሙያ መሰላል ወደሚቀጥለው ከፍ ያለ የሙያ መሰላል ለማደግ የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡-

ሀ) የሙያ መሰላል ዕድገት ዝርዝር ከመውጣቱ በፊት በደረጃው በተሞላለት የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቶች በሁሉም ቢያንስ አጥጋቢ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት ያስመዘገበ፤

ለ) በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ የሚሰጠውን አግባብነት ያለው ሥልጠና የወሰደ፤

ሐ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፳ የተመለከተውን ለደረጃው የተወሰነውን የቆይታ ጊዜ ያሟላ፤

መ) ለደረጃው የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ የሚሰጠውን የብቃት ማረጋጫ ፈተና ያለፈ እንዲሁም፤

ሠ) በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የተስማሚነት ማጣሪያ ያለፈ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪(ለ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ “ዝቅተኛ” አፈጻጸም ምዘና ውጤት በማምጣቱ ምክንያት የሙያ መሰላል እድገት ያለፈው የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ በቀጣይ ሁለት ተከታታይ የአፈጻጸም ምዘናዎች ላይ “አጥጋቢ” ውጤት ካገኘ ለሚቀጥለው የሙያ መሰላል እድገት ብቁ ይሆናል፡፡

፭/ ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ ተጨማሪ መስፈርቶችን በመመሪያ ሊወስን ይችላል፡፡

eligible for promotion to the next higher career ladder by fulfilling the criteria stated under this Regulation.



2/ Career ladder promotion shall be given primarily based on the performance evaluation result of the employee.

3/ For the purpose of being promoted from one career ladder to the next higher ladder the following criteria must be fulfilled by any diplomatic service officer who has:

a) scored at least a “satisfactory” grade in all evaluations on a rank preceding the announcement of promotion;

b) taken the relevant training provided by the diplomatic service sector;

c) served the number of year of service stated under Article 20 of this Regulation;

d) passed the competence certification exam of the position given by the Examination Administration Board;

e) passed the suitability verification conducted in accordance with sub-article (1) of Article 14 of this Regulation.

4/ Without prejudice to sub article 2(b) of this article, a diplomatic service officer who has not been promoted for reasons of scoring “low” on his evaluation shall be eligible for career ladder promotion by scoring at least “medium” in two consecutive performance evaluations.

5/ The Ministry may provide additional criteria by a

https://chilot.me



**፲፱. <u>በሙያ መሰላል የሚደረግ ዕድገት አፈፃፀም</u>**

፩/ የሰው ሀብት ማኔጅመንት ከዕቅድና በጀት ዳይሬክቶሬት ጀኔራል ጋር በመመካከር በየበጀት ዓመቱ መጀመሪያ በአዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለሙያ መሰላል ዕድገት ብቁ የሆኑ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞችን ዝርዝር እና ሊያድጉ የሚችሉበትን ደረጃዎች ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሥራ አመራር ምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

፪/ በሚሲዮኖች የሚሰሩ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች የፈተናዎች አስተዳደር ቦርድ የሚሰጠውን የብቃት ማረጋጫ ፈተና ባሉበት ሚሲዮን ሆነው እንዲፈተኑ ይደረጋል።

፫/ የሰው ሀብት ማኔጅመንት ፈተናውን ቢያንስ በአጥጋቢ ውጤት ያለፉ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞችን የሙያ መሰላል ዕድገት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ተፈፃሚ ያደርጋል።

**፳.<u>በሙያ መሰላል የሚደረግ ዕድገት የአገልግሎት ዘመን</u>**

፩/ ማንኛውም ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ከአንድ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ምድብ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለማደግ በዋናነት በሥራ ውጤቱ የሚመዘን ሆኖ የሚከተለውን በየደረጃው የሚጠበቀውን የቆይታ ጊዜ ማሟላት ይኖርበታል፣

ሀ) ከአታሼ ደረጃ ወደ ሦስተኛ ጸሐፊ.............ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፣

ለ) ከሦስተኛ ጸሃፊ ወደ ሁለተኛ ጸሐፊ..........ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፣

ሐ) ከሁለተኛ ጸሃፊ ወደ አንደኛ ጸሐፊ.........ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፣

መ) ከአንደኛ ጸሃፊ ወደ አማካሪ II.................ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፣

**19. <u>Implementation of a Career Ladder Promotion</u>**

1/ Pursuant to the Proclamation and this Regulation, the Human Resource Management in consultation with the Plan and Budget Directorate General, shall submit to the Management Council the list of diplomatic service officers eligible for promotion, the positions they shall be promoted in every budget year with its recommendation and implement upon the Council's approval.

2/ Diplomatic service officers working in missions abroad shall take the competence certification exam of the Examinations Administration Board at the missions they work at.

3/ The Human Resource Management shall implement, within 30 days, the promotion of diplomatic service officers who scored at least a "satisfactory" result in the examination.

**20. <u>Duration of service for Career Ladder Promotion</u>**

1/ Any permanent diplomatic service officer shall mainly be evaluated based on his performance and shall fulfill the following years of service to be promoted from one diplomatic service ladder to the next higher ladder:

a) from Attaché to Third Secretary…………two years and six months;

b) from third secretary to second secretary…two years and six months;

c) from second secretary to first secretary…two years and six months;

https://chilot.me



፱ሺ፭፻፶፱

ሰ) ከአማካሪ II ወደ አማካሪ I.........ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፤

ረ) ከአማካሪ I ወደ ሚኒስትር አማካሪ II........ሁለት ዓመት ከስድስት ወር፤

ሠ) ከሚኒስትር አማካሪ II ወደ ሚኒስትር አማካሪ I.....ሦስት ዓመት፤

ሸ) ከሚኒስትር አማካሪ I ወደ ሚኒስትር.......ሦስት ዓመት፤

ቀ) ከሚኒስትር ወደ ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር….ሦስት ዓመት::

፪/ ማንኛውም ቋሚ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኛ ከአንድ የቆንስላ አገልግሎት ምድብ ደረጃ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ለማደግ የሚከተለውን የአገልግሎት ዘመን ማሟላት ይኖርበታል:-

ሀ) የረዳት ቆንሱል ምድብ... የአንደኛ ጸሐፊ ደረጃ አቻ የአገልግሎት ዘመን፤

ለ) ከረዳት ቆንሱል ወደ ምክትል ቆንሱል... የአማካሪ I ደረጃ አቻ የአገልግሎት ዘመን፤

ሐ) ከምክትል ቆንሱል ወደ ቆንሱል.... የሚኒስትር አማካሪ I ደረጃ አቻ የአገልግሎት ዘመን፤

መ) ከቆንሱል ወደ ቆንሱል ጄኔራል..... የባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ደረጃ አቻ የአገልግሎት ዘመን::

**፳፩. <u>በልዩ ሁኔታ የሚሰጥ ፈጣን የሙያ መሰላል ዕድገት ሥርዓት</u>**

፩/ በአዋጁ አንቀጽ ፳፯(፪) መሠረት የሚሰጥ ማንኛውም ፈጣን የሙያ መሰላል ዕድገት የሚኒስቴሩን ፍላጎትና መሠረት ያደረገ እና በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ሚኒስቴር የወጣውን መመሪያ ተከትሎ የሠራተኛውን የላቀ አፈጻጸም መሠረት ያደረገ ይሆናል::

d) from first secretary to Counselor II………two years and six months;

e) from Counselor II to Counselor I…………two years and six months;

f) from Counselor I to Minister Counselor II…two years and six months;

g) from Minister Counselor II to Minister Counselor I……..three years;

h) from Minister Counselor I to Minister…three Years;

i) from Minister to Minister Plenipotentiary ….three Years.

2/ any permanent diplomatic service officer shall fulfill the following service year to be promoted from one consular service ladder to the other፡

a) vice consul……Equivalent to the service required to attain the rank of a first secretary;

b) from vice consul to deputy consul…..Equivalent to the service required to attain the rank of Counselor I;

c) from deputy consul to consul….Equivalent to the service required to attain the rank of Minister counselor I;

d) from consul to consul general… equivalent to the service required to attain the rank of Minister Plenipotentiary.

**21. <u>Special Procedure for Accelerated Career Ladder Promotion</u>**

1/ any accelerated promotion granted pursuant to Article 27(2) of the Proclamation shall be based on the need of the Ministry and on the employee's "outstanding" performance evaluation result pursuant to the directives issued by the Ministry of Public Service and

https://chilot.me



፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ፈጣን ፱ሺ፭፻፷ መሰላል ዕድገት ለማግኘት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፰(፪) ከፊደል ተራ (መ) በስተቀር የተቀመጡትን ሌሎች መስፈርቶች ማሟላት አለበት፡፡

፫/ ሁሉም የሥራ ክፍሎች ፈጣን የሙያ መሰላል ዕድገት ለማግኘት መስፈርቱን የሚያሟሉ ሠራተኞችን በመለየት ከውሳኔ ሀሳብ ጋር ለሰው ሀብት ማኔጅመንት ያቀርባሉ፡፡ የሰው ሀብት ማኔጅመንት የተጠቃለለ የውሳኔ ሀሳብ ለሥራ አመራር ምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ዕድገቱን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**፳፪. <u>ዕድገት ከሚያገኙ ሠራተኞች ዝርዝር በጊዜያዊነት ስለመሠረዝ</u>**

፩/ ማንኛውም ቋሚ የዲኘሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ በሚከተሉት ምክንያቶች የሙያ መሰላል ዕድገት ከሚያገኙ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ዝርዝር ውስጥ በጊዜያዊነት ሊሰረዝ ይችላል:-

ሀ) የተስማሚነቱ ሁኔታ አጠራጣሪ ሲሆን፤

ለ) ከባድ የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደበት መሆኑ ሲረጋገጥ፤

ሐ) ለሙያ መሰላል ዕድገት ብቁ የሆኑ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ዝርዝር ከመውጣቱ በፊት ከተከናወኑ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቶች መካከል በአንዱ ዝቅተኛ ውጤት ሲያስመዘግብ፡፡

፪/ ማንኛውም ቋሚ የዲኘሎማቲክ አገልግሎት ዘርፍ ሠራተኛ የሙያ መሰላል ዕድገት ከሚያገኙ የዲፕሎማቲክ አገልግሎት ሠራተኞች ዝርዝር ውስጥ በጊዜያዊነት እንዲወጣ የሚደረገው በሥራ አመራር ምክር ቤቱ ሲወሰን ብቻ ይሆናል፡፡

Human Resource Development.

2/ in order to get the accelerated ladder promotion stipulated in sub-article (1) of this A 9560 diplomatic service officer shall fulfill all requirements stipulated under sub-article (2) of Article 18 of this Regulation except paragraph (d).

3/ each sector shall identify list of diplomatic service officers eligible for accelerated career ladder promotion and submit to the Human Resource Management with recommendation. The Human Resource Management shall submit a summary of the recommendations to the management council and it shall implement the promotion up on approval.

**22. <u>Temporary removal from the list of employees eligible for promotion</u>**

1/ any permanent diplomatic service sector officer may be removed from the list of employees eligible for promotion when:

a) his suitability is in question;

b) it is proved that a rigorous disciplinary measure was taken against him;

c) he scored low performance in one performance evaluation that took place prior to the notification of the list of diplomatic service officers eligible for career ladder promotion.

2/ any permanent diplomatic service officer shall only be removed from the list of diplomatic service officers eligible for career ladder promotion only if

https://chilot.me



**፳፫. <u>የሙያ መሰላል የደረጃ ዕድገት ስለሚሰረዝበት ሁኔታ</u>**

፩/ በዲሲፕሊንና በመወንጀል የሚያስከትለው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሀሰት ማስረጃ በማቅረብ ወይም በማጭበርበር ወይም ሕግን በመተላለፍ የተገኘ የደረጃ ዕድገት እንዳልተሰጠ ይቆጠራል፡፡

፪/ የሀሰት ማስረጃ በማቅረብ ወይም በማጭበርበር ወይም ሕግን በመተላለፍ የተሰጠ የደረጃ ዕድገት የሀሰት ማስረጃ፣ ማጭበርበሩ ወይም የሕግ ጥሰቱ በታወቀበት በማናቸውም ጊዜ ሊሰረዝ ይችላል፡፡

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>ስለውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኞች</u>**

**<u>ልዩ ልዩ መብቶችና ጥቅማ ጥቅሞች</u>**

**፳፬. <u>ስለሚከፈሉ ልዩ ልዩ አበሎች</u>**

፩/ በሚሲዮን የሚመደብ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ ከመደበኛ ደሞዙ በተጨማሪ የሚከተሉት ልዩ ልዩ አበሎች ይከፈሉታል፤

ሀ) የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛው ከእነቤተሰቡ ከዋናው መሥሪያ ቤት ወደ ሚሲዮን፣ ከሚሲዮን ወደ ሚሲዮን ወይም ከሚሲዮን ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ሲዛወር የመጓጓዣና የጓዝ ማጓጓዣ አበል፤

ለ) የኑሮ መደጎሚያ አበል፤

ሐ) የቤት ኪራይ አበል፡፡

፪/ በአዋጁ አንቀጽ ፴፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚሲዮን መሪ፣ የቆንስላ ጽሕፈት ቤት ወይም የንግድ ጽሕፈት ቤት መሪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሱ

the Management Council passes the decision to do so.



**23. <u>Cancellation of a Career Ladder Promotion</u>**

1/ Without prejudice to disciplinary and criminal liability, a promotion obtained as a result of forged document or deceitful practice or in contravention of the law shall be *void*.

2/ any promotion granted as a result of forged document or deceitful practice or in contravention of the law may be cancelled at any time when such forgery, deceitful practice or contravention of law is discovered.

**<u>PART FIVE</u>**

**<u>ALLOWANCES AND BENEFITS TO FOREIGN SERVICE OFFICERS</u>**

**24. <u>Allowances</u>**

1/ The Foreign Service officer assigned in the missions shall receive the following allowances in addition to his salary:

a) travel allowance and relocation of goods allowance when a Foreign Service officer is transferred from the head office to the mission or from one mission to another mission or from mission to the head office;

b) living cost allowance;

c) house rent allowance.

2/ Without prejudice to Article 37 of the Proclamation, the head of a diplomatic mission or head of consular

https://chilot.me



ኀከፈሉታል፡፡

**፳፭.** **<u>ስለጤና መድህን ሽፋን</u>**

ማንኛውም በሚሲዮን የተመደበ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ፣ የትዳር ጓደኛው እና ፳፩ ዓመት ያልሞላቸው ልጆች የጤና መድን ዋስትና በሚኒስቴሩ ይሸፈናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፮.** **<u>በቅሬታ ሰሚ ቦርድ የሚታዩ ጉዳዮች</u>**

በአዋጁ አንቀጽ ፶(፩)(ሐ) የተቋቋመው የቅሬታ ሰሚ ቦርድ የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚያቀርቡትን ቅሬታ አጣርቶ የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስትሩ ያቀርባል፤

፩/ ከመብቶችና ጥቅሞች አጠባበቅ፤

፪/ ከምደባ፣ ጥሪና ደረጃ ዕድገት አሰጣጥ፤

፫/ ከሥራ አፈጻጸም ምዘና እና

፬/ በአዋጁና በዚህ ደንብ አፈጻጸም፡፡

**፳፮.** **<u>የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት</u>**

፩/ ማንኛውም የውጭ ግንኙነት አገልግሎት ሠራተኛ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳፮ በተጠቀሱት ጉዳዮች፣ በአዋጁ እና በዚህ ደንብ አፈፃፀም ላይ ያለውን ማንኛዉም ዓይነት ቅሬታ ለቅርብ አለቃው ወይም ለሚመለከተው የሥራ ኃላፊ አቅርቦ በሚሰጠው ምላሽ ካልረካ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ለቅሬታ ሰሚ ቦርድ የማቅረብ መብት አለው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የቅሬታ ማመልከቻውን ማቅረብ ያልቻለ ሰራተኛ ከአቅም በላይ የሆነው ምክንያት በተወገደበት በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ማመልከቻውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

office or trade office shall get the allowances provided under paragraph (a) and (b) of sub-article (1) of this Article.

**25. <u>Health Insurance</u>**

The Ministry shall cover health insurance of any Foreign Service officer, his spouse and children below the age of 21 while being assigned in a mission.

## PART SIX

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**26. <u>Matters Considered by Grievance Board</u>**

The Grievance Board established in accordance with Article 50(1)(C) of the Proclamation shall investigate complaints made by foreign service officers and submit recommendation to the Minister regarding matters relating to:

1/ the protection of rights and benefits;

2/ placement, recall, career ladder promotion;

3 /performance evaluation;

4/ the implementation of the Proclamation and this Regulation.

**27. <u>Procedures for submission of Grievance</u>**

1/ A Foreign Service officer who is not satisfied with the response by his immediate supervisor or with the concerned official, on issues under Article 26 of this Regulation, on the implementation of the Proclamation and this Regulation, has the right to submit a petition to the Grievance Board within ten working days from the response.

2/ An officer who is unable to submit his petition within the period specified under sub-article (1) of

https://chilot.me





፫/ የቅሬታ ሰሚ ቦርዱ የቀረቡለትን ቅሬታዎች በማጣራት የምርመራውን ውጤትና የውሳኔ ሀሳብ የያዘ ሪፖርት ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ፲፭ የሥራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለሚኒስትሩ ያቀርባል።

፬/ ሚኒስትሩ ወይም ወኪሉ የቅሬታ ሰሚ ቦርድ ሪፖርት በደረሰው ከአስር የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የቦርዱን ውሳኔ ማፅደቅ ወይም ቦርዱ ከቀረበለት የውሳኔ ሃሳብ የተለየ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ቦርዱ ጉዳዩን እንደገና እንዲመረምር ለማዘዝ ይችላል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሰረት የተሰጠ ውሳኔ ለአመልካቹ በጽሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል።

**፳፰.** **<u>መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>**

ሚኒስቴሩ ይህን ደንብ ለማስፈጸም የሚያስች መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

**፳፱.** **<u>የሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>**

፩/ ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ እና አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

፪/ የዚህ ደንብ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ ደንብ እና ተከትለው በሚወጡ መመሪያዎች ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ እና አዋጁን ተከትለው የወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በሚሚያነት ተፈፃሚ ይሆናሉ፡

this Article due to reasons that are beyond his control, may submit his petition within ten working days after such reasons has passed.



3/ The Board shall submit a report containing its findings and recommendations to the Minister not later than 15 working days from the date of receipt of the petition.

4/ The Minister or the official delegated by him may, within ten working days from the date of receipt of the Board's report, approve the recommendation of the Board or, give a decision different from the recommendation of the Board or instruct the Board to further review the case.

5/ The decision passed in accordance with sub-article (4) of this Article shall be communicated to the petitioner in writing.

**28. <u>Power to Issue Directives</u>**

The Ministry may issue a directive necessary for the implementation of this Regulation.

**29. <u>Application of other Laws</u>**

1/ No regulations, directive or practice that is inconsistent with the provisions of this Regulation shall be applicable with respect to matters covered under this Regulation.

2/ Without prejudice to the provision of sub-article (2) of this Article, the relevant provisions of the Federal Civil Servants Proclamation and Regulations and Directives issued there under shall be applicable-with respect to matters not covered by this Regulation and directives issued hereunder.

https://chilot.me



**፴.**<u>**ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**</u>

ይህ ደንብ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፳፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

**30.** <u>**Effective Date**</u>

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 7th day of March 2017**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me